# በዓለም አቀፍ ደረጃ ክብርና ዝናን የተጎናፀፈው ሠራዊታችን

## (ክፍል ሁለት)

**ሱራፌል ዓለሙ** 12-25-14

መከላከያ ሰራዊታችን በሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ ብቻ በህዝቡ እየተደገፈ፣ ራሱን በራሱ እያስተማረና ከተግባር ፍፃሜዎቹ እየተማረና ይበልጥ ራሱን እያጠናከረ ለዛሬ ጠንካራ ስብዕናው የበቃ ኃይል ነው። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ሰራዊቱ ከተግባራዊ ተሞክሮዎቹ ራሱን እያነፀ ባይመጣ ኖሮ ዛሬ ላይ ለሚገኝበት ዓለም አቀፍ ክብር ባልበቃ ነበር።

ሆኖም ሰራዊቱና አመራሩ እጅና ጓንት ሆነው በመስራት እንዲሁም ሁሉም በየደረጃው የተሰጠውን ሀገራዊ ተልዕኮ በብቃትና ህዝባዊነቱን አንግቦ በፍፁም ሀገራዊ ስሜት የሚፈፅም መሆኑ ዛሬ በተለያዩ ወታደራዊ ድረ-ገፆች ሳይቀር ጥንካሬውና አቅሙ በስፋት እንዲነገርለት ምክንያት ሆኗል። እስቲ አሁንም ይህን የሰራዊታችንን ዝና እና ተቀባይነትን ካጎለበቱት ፍፃሜዎች መካከል ጥቂቶቹን እየነቀስን እንመልከት።...

## የቅርብ ጊዜ ፍፃሜዎች

እንደሚታወቀው በሱዳን ምዕራባዊ ክፍል በሚገኘው የዳርፉር ግዛት በአማፂያንና በሀገሪቱ መንግስት መካከል በተቀሰቀሰው ግጭት ሳቢያ፤ በአስር ሺህዎች የሚጠጉ ሰዎች መሞታቸውንና ከሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ተሰድደዋል። ይህን ቀውስ ተከትሎም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ህብረት ጥምር ኃይል (UNAMID) በዳርፉር እንዲሰፍር ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

ሀገራችንም ሠራዊት እንድታዋጣ የአፍሪካ ህብረትና ተመድ ያቀረቡላትን ጥያቄ በተለመደው ፅኑ የሠላም መርህዋ መሠረት ጥሪውን በመቀበል ደረጃ በደረጃ 5 ሺህ ሠራዊት ወደ ስፍራው ለመላክ እንዲሁም ለተልዕኮው የሚያገለግሉ አምስት ታክቲካል ሄሊኮፕተሮችን ለማሰማራት መወሰኗ ይታወሳል፡፡ በውሳኔው መሰረትም የመጀመሪያው ዙር የሠላም አስከባሪ ኃይል በ2000 ዓ.ም ወደ ዳርፉር አቅንቶ ግዳጁን በወንድማማች እና ህዝባዊ ፍቅር

በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ የዳርፉሩን የሠራዊታችን ተልዕኮ ቀደም ካሉት ግዳጆች ልዩ የሚያደርጉት ሁለት ጉዳዮች መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል።

አንደኛው ስምሪቱ የተካሄደው ረጅም ድንበር፣ የተፈጥሮ ሀብትና ተመሳሳይ ብሔረሰቦችና ሃይማኖቶችን አብረናት በምንጋራው ጎረቤታችን ሱዳን ውስጥ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ሠራዊታችን ከዚህ ቀደም ተሳትፎ ከሚያደርግበት የእግረኛ፣ የስታፍና ወታደራዊ ታዛቢ ተልዕኮ ባሻገር በትራንስፖርት በሁለገብ የሎጀስቲክስ አገልግሎት፣ በቃኚ፣ በአየር ኃይል እና በጥልቅ ጉድጓድ የውሃ ቁፋሮ ግዳጆች  መሰማራቱ ነበር፡፡ እርግጥ እነዚህን ተጨማሪ ተልዕኮዎች ሠራዊቱ በአሃድ እና በሻምበል ተደራጅቶ እንዲፈጽም በመንግስታቱ ድርጅትና በአፍሪካ ህብረት ጥምር ኃይል የዳርፉር ተልዕኮ (UNAMID) የተሰጠው ሠራዊታችን፣ በዓለም አቀፉ የሠላም ማስከበር ግዳጆች የሚያከናውነውና በማከናወን ላይ የሚገኘው ተግባር ምን ያህል ተቀባይነትና አመኔታ እያገኘ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ተቋሙ በውስጡ በሚያካሂደው ተቋማዊ የለውጥ እንቅስቃሴ በዘርፉ ያለንን የተወዳዳሪነት ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሰዱና ለተወዳዳሪነት ለሚያበቁ ቅድመ ዝግጅቶች ልዩ ትኩረት በመስጠቱ ነው፡፡ በሠላም ማስከበር ስራ ላይ የሠራዊታችን  አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እና ተወዳዳሪ እየሆነ መጥቷል። ከዚሁ ጋር ለህዝብ ወግኖ የሚያከናውናቸው ተግባሮቹ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ቀልብ እየሳበ መምጣቱን ሌላው ምክንያት ነበር፡፡

ያም ሆነ ይህ ሰራዊታችን በየተሰማራባቸው የግዳጅ ቀጣናዎች አካባቢ  ወንድም ለሆነው የሱዳን ህዝብ በነጻ ህክምና በመስጠት፣ ተፈናቃዮች በታጣቂዎች ጥቃት እንዳይደርስባቸው በመከላከል፣ አብዛኛው ክፍሉ በረሃማ በሆነው የዳርፉር ግዛት ውስጥ ውሃ ቆፍሮ በማውጣት ህብረተሰቡንና እንስሳቶቹን ከእንግልት በመታደግ እንዲሁም ከዕለታዊ ቀለቡ ቀንሶ ችግረኞችን በመርዳት ወዘተ...ህዝባዊ ተግባራትን አከናውኗል። በዚህም በአካባቢው ማህብረሰብና በመንግስት ኃላፊዎች እኩል ተቀባይነትንና አድናቆትን ሊያገኝ ችሏል፡፡ እስሁን ድረስም በህዝቡ እየተመሰገነ ተግባሩን በመወጣት ላይ ይገኛል።

የደቡብ ሱዳንን ህዝብ - ውሳኔን ተከትሎ የደቡቡ እና የሰሜኑ መንግስታት የነዳጅ ሀብት ባለቤት የሆነችውን አብዬ ግዛትን አስመልክቶ መግባባት ላይ ሊደርሱ  አልቻሉም፡፡ በዚህም ሳቢያ በግዛቲቱ ግጭት በመቀስቀሱ የሰው ህይወት ጠፍቷል፡፡  የአካባቢው ነዋሪም ቀዬውን

ትቶ ተሰድዷል፡፡ ይህን ሁኔታ የተገነዘበው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤ በአካባቢው ሠላም አስከባሪ ኃይል እንዲሰማራ ሃሳብ ያቀርባል። በመንግስታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት 15ቱ አባል ሀገራትም 4200 የኢትዮጵያ ሠራዊት በአብዬ ተሰማርቶ የህዝቦችን ሠላም በብቸኝነት እንዲጠብቅ ያለምንም ተቃውሞ በሙሉ ድምፀ- ውሳኔ ማሳለፋቸው ይታወቃል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ አስገራሚው ጉዳይ ሁሉም የፀጥታው ምክር ቤት አባል ሀገራት ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ ያለ አንዳች ልዩነት ለኢትዮጵያ ሠራዊት ይሁንታ መስጠታቸው ብቻ አይደለም፡፡ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ሁለቱ ሱዳኖችም (ደቡብና ሰሜን) የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በአብዬ ግዛት ብቸኛው የሠላም አስከባሪ ኃይል ሆኖ እንዲሰማራ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን መግለጻቸውን ሁኔታውን አስደናቂ ያደርገዋል። ሦስቱም አካላት (የፀጥታው ምክር ቤት፣ ሰሜንና ደቡብ ሱዳን) ያለምንም ማመንታት አንድን ሀገር በሠላም ማስከበር ተልዕኮ እንድትሰማራ ሲወስኑ፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ነው፡፡ ሠራዊታችን ለአብዬ የሠላም ማስከበር ተልዕኮ በሁሉም ወገኖች አመኔታ ያገኘው ያለ ምክንያት አይደለም። የመንግሥታችን ሠላም ወዳድነት፣ የሚመራባቸው የሠላም ፖሊሲና ስትራቴጂዎች እንዲሁም የሚያከናውናቸው ተግባራት ለማንም ያልወገኑና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችንና ዲፕሎማሲያዊ ስራዎች ውጤትም ናቸው፡፡

መከላከያ ሠራዊታችንም ህዝብና መንግሥት የሰጡትን ተልዕኮ በቁርጠኝነት ተቀብሎ በተሰማራባቸው የግዳጅ አካባቢዎች ሁሉ በጠንካራ ህዝባዊ ወገንተኝነት ተግባሩን በብቃት፣ በጀግንነትና በሚያኮራ ሁኔታ መፈጸሙ በመንግሥታቱ ድርጅትም ይሁን በሁለቱም ተቀናቃኝ ወገኖች ጽኑ እምነትንና አክብሮትን ያጐናፀፈውና ብቸኛው ተመራጭ ሠራዊት ሊያደርገው ችሏል። ሠራዊታችን በግዳጅ አፈጻጸም ብቃቱ በሦስቱም አካላት በተሰጠው አመኔታ መሠረት፤ የመጀመሪያው ዙር የኢትዮጵያ የሠላም አስከባሪ ሠራዊት ሐምሌ 9 ቀን 2003 ዓ.ም ወደ አብዬ ግዛት አምርቶ በተለመደ ህዝባዊ ባህሪው ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር ተቀራርቦ በመስራት ግዳጁን በውጤታማነት በመፈጸም ላይ ይገኛል።

መንግስትና ህዝብ በሰጡት አደራ መሠረት ሠራዊታችን ባከናወናቸው ሠላም ተኮር ተግባራት በተለይም ባለፉት የድል ዓመታት በዘርፉ ተወዳዳሪ ለመሆን በሰራቸው ጠንካራ ሥራዎች የበርካታ የአፍሪካ ህዝቦችና መንግስታት በሙሉ እምነት እንዲቀበሉት አድርጓል። በአፍሪካ ህብረት የሠላምና የፀጥታ ምክር ቤት ከሚያቅፋቸውና በአምስቱ የአፍሪካ

ቀጣናዎች ከተቋቋሙት የተጠንቀቅ ብርጌዶች ውስጥም፣ ሀገራችንን የሚያቅፈው የምስራቅ አፍሪካ የተጠንቀቅ ኃይል (ቀደም ሲል ብርጌድ እንደነበር ልብ ይሏል!) ጠቅላይ ሰፈሩ አዲስ አበባ ውስጥ እንዲሆን መወሰኑና የመጀመሪያውን ዙር የኃይል አዛዥነት ስፍራ ለኢትዮጵያና ለሠራዊቷ መሰጠቱ የዚህ ዕውነታ አንድ መገለጫ ነው ማለት ይቻላል። ሌላኛው የሰራዊታችን የሰላም ማስከበር ተልዕኮ በቅርቡ በአፍሪካ ህብረት ጠያቂነት በሶማሊያ ከአሚሶም ጋር የተቀላቀለበት ነው። በወርሃ ታህሳስ 2006 ዓ.ም በሶማሊያ የሚገኘውን የአፍሪካ ሠላም አስከባሪ ኃይልን ለማጠናከር የአሚሶምን (AMISON) ተልዕኮ እንዲቀላቀል ለሀገራችን በቀረበላት ጥሪ መሰረት፣ 4 ሺህ 403 የመከላከያ ሠራዊታችን አባላት ወደ ስፍራው ተሰማርተዋል።

ተልዕኮአቸውንም ቀጣና ሶስትንና አራትን በመረከብ ኃላፊነት በተሞላበት መንፈስ መወጣት መጀመር ብቻ ሳይሆን በአልሸባብ ላይ ድልን ተቀናጅቶ በርካታ ከባቢዎችን መቆጣጠር ችሏል፡፡ በነገራችን ላይ ይህ ተጨማሪ ተልዕኮ የሠራዊታችን ቁጥር በሠላም ማስከበር ተልዕኮ ያለውን ተሳትፎ ቁጥር ወደ 11 ሺህ 994 ከፍ ያደርገዋል፡፡

ሠራዊታችን የሠላም አምባሳደር ሆኖ ወደ ጎረቤት ሶማሊያ የአሚሶምን ግዳጅ ተቀብሎ ሲንቀሳቀስ ያነገባቸውን ዋነኛ ተልዕኮዎች ገቢራዊ እያደረገ ነው። እነርሱም በተረከባቸው ቀጣናዎች ያለውን ሰላም አስተማማኝ የማድረግ፣ ከአሚሶም እና በእርሱ ስር ካሉ የሠላም አስከባሪ ሃይሎች ጋር በመጣመር በሶማሊያ የመሸጉ ሽብርተኞችን መደምሰስና ማጥፋት እንዲሁም ከህዝቡ ጋር በመሆን የተረጋጋ የመስተዳድር መዋቅሮችን እንዲፈጠሩ መስራት ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎቹ እንዳደረገው ሁሉ፣ በሶማሊያም ህዝቡ ራሱን የሚያስተዳድርበትንና የፀጥታ መዋቅሩን በባለቤትነት የሚመራበትን ሁኔታ የመፍጠር፣ የሶማሊያ መንግስትን የፀጥታ ኃይል የተሻለ ብቃት እንዲኖረው ለማድረግ የማሰልጠን፣ የማስታጠቅ፣ የማደራጀት፣ የራሱንም አቅም እንዲገነባ የሚያስችሉ ተግባራትን በመፈፀም ላይ ይገኛል፡፡

እዚህ ላይ ሰሞኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ሰራዊቱ በአሚሶም ውስጥ ያለውን ወሳኝ እንቅስቃሴ አስመልክተው “ሰራዊቱ ከሶማሊያ የፀጥታ ሃይሎች ጋር በመሆን 65 በመቶ የሚሆነውን ቦታ አልሸባብ ነፃ ማውጣት ችሏል” በማለት የገለፁት ዕውነታ፣ ሰራዊቱ ከላይ የጠቀስኳቸውን ተልዕኮዎቹን ደረጃ በደረጃ እያከናወነ መምጣቱን የሚያመላክት መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

እርግጥ ሰራዊቱ ቀደን ሲል ከጠቀስኳቸው ተግባራቱ ጎን ለጎንም በተሰጠው ቀጣና ውስጥ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የማቀላጠፍና በዚህም ለዕርዳታ ሰጪዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የዕለት ደራሽም ሆነ ሌሎች ሰብዓዊ ተግባሮች በተገቢው ሁኔታ እንዲደርሱ ማድረግ፣ መንግስታችን በሚደግፈው ውስን ሀብትም ጉልበቱንና ዕውቀቱን በማስተባበር አንዳንድ ማህበራዊ ተቋማትን ለአካባቢውን ህብረተሰብ የመገንባት ተልዕኮን ያነገበ ነው፡፡

ለነገሩ ሠራዊታችን ከዚህ ቀደም በነበሩ የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎች ካካበተው የዳበረ ልምድ በመነሳት ተልዕኮውን በአስተማማኝ እንደሚወጣ ጥርጥር ያለው ጉዳይ አይመስለኝም፡፡ ይህን የምልበት ዋነኛ ምክንያት ሰራዊቱ ከሌሎች ሀገሮች የላቀ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ስለታጠቀ አይደለም– ትጥቁ ህዝባዊነቱ ብቻ ስለሆነ እንጂ፡፡ እርግጥ የሰራዊታችን ዋናው ትጥቅ ህዝብን ማክበሩ እና እነሱም እርሱን የሚያከብሩት በመሆናቸው ተልዕኮው እንዲያሳካ ሁሌም ከጎኑ የሚሰለፉ በመሆናቸው ነው፡፡ እናም ሠራዊታችን በፅኑ ህዝባዊ መሰረት የተገነባ የሰላም ሃይል ስለሆነ፤ ትጥቁም ሆነ ስንቁ የማይነጥፈው ህዝባዊ ወገንተኝነቱ እና የግዳጅ አፈጻጸም ብቃቱ ብሎም ዲሲፕሊኑ መሆኑን እዚህ ላይ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ህገ-መንግሥቱን መሠረት አድርጎ የተገነባው መከላከያ ሠራዊታችን በተሳተፈባቸው የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎች ሁሉ፤ እያንዳንዱ የሠራዊቱ አባል ከዓለም አቀፍ ተልዕኮው ጐን ለጐን የሀገራችንን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዘቦች ወግ፣ ባህልና ትውፊቶችን በማስተዋወቅ የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ገጽታ የመገንባት ተግባርን አከናውኗል። ከዚህ በተጨማሪም፤ በሀገራችን ውስጥ እየተመዘገበ ስላለው ልማት፣ ስለተፈጠረው አስተማማኝ ሠላምና ስር እየሰደደ ስላለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በአጠቃላይ የሃገራችን የኀዳሴ ጉዞና ስኬቷን ለሌሎች ሠላም አስከባሪ ሀገር ሠራዊቶች እንዲሁም ተልዕኮውን ለሚያከናውንበት ሀገር፣ ህዝብና መንግሥት በማስረዳት የአምባሳደርነት ሚና ተጫውቷል። ወደፊትም ይኸው የህዝባችን ኩራት የሆነው ሰራዊት ይህን ተግባሩን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ለመገመት ነብይ መሆን የሚያስፈልግ አይመስለኝም።

የኢፌዴሪ መንግስት የገነባውና በመገንባት ላይ ያለው ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ ብቻ ሣይሆን፤ ልማታዊም ጭምር በመሆኑ ሠራዊታችንም የዚሁ ነፀብራቅ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ፈጣንና ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማት ለመከላከያ ግንባታ ወሣኝ መሠረት ነው፡፡ የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ባደገ ቁጥር ለመከላከያ የሚመደበው በጀትም የዚያኑ ያህል

መጨመሩ አይቀርም፡፡ ይሁንና የወታደራዊ ሣይንስ ሊቆች እንደሚያስረዱት የአንድ ሀገር መከላከያ በጀት ከሀገሪቱ አጠቃላይ በጀት ከሁለት በመቶ በላይ መብለጥ የለበትም። ነገር ግን እንደ አሜሪካ ያሉ ያደጉ ሀገሮች እንኳን ቢሆኑ ለመከላከያ የሚያወጡትን እያንዳንዱን ገንዘብ ለመቀነስ እየጣሩ ወጪያቸው ግን ከአጠቃላይ የሀገራቸው ገቢ አኳያ ከሁለት በመቶ በላይ መሆኑ አልቀረም፡፡

ለነገሩ እንደ እኛ በማደግ ላይ ያለ ሀገር አብዛኛውን ሀገራዊ ገቢ ለመሠረተ ልማት፣ ለትምህርት፣ ለጤና... ወዘተ ማዋል ካልቻለ ፈጣንና ተከታታይ የምጣኔ ሐብት ዕድገትን ሊያስመዘግብ አይችልም፡፡ ከዚህ የህዝብን ተጠቃሚነት ከሚያረጋግጥ ዕውነታ በመነሳትም የሀገሪቱን መከላከያ በጀት እንኳንስ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያለውን (ማለትም ከአጠቃላይ ሀገራዊ ገቢ ሁለት በመቶ) ሊጠጋ ቀርቶ ከአንድ በመቶ በታች እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ የሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው ኢኮኖሚው ሊያቀርበው የሚችለው ትርፍ ሃብት ከኢኮኖሚው ስፋት አንፃር ሲታይ አነስተኛ በመሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መከላከያ ሠራዊታችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የተመደበለትን በጀት በቁጠባ አብቃቅቶ የመጠቀም ባህሉ በከፍተኛ ደረጀ በማደጉ ነው፡፡

የዳበረና የተሻለ የኢኮኖሚ ልማት ያለው ሀገር ለሠራዊቱ የሚመድበው በጀት ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል አያጠያይቅም፡፡ በዚያኑ ልክ ደግሞ በማደግ ላይ ያለ ኢኮኖሚ ያለው ሀገር በውስጡ የሚያከናውናቸው በርካታ የህዝብን ህይወት የሚለውጡ ጉዳዩች በመኖራቸው በተነፃፃሪነት ካደጉት ሀገሮች እኩል የመከላከያውን በጀት ሊመድብ አይችልም። ምክንያቱም ህዝቡ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ገቢ በነፍስ ወከፍ የሚደርሰው ገቢ ቢሰላ መከላከያውን ለመገንባት የሚያስችለው የተትረፈረፈ ሃብት ሊኖረው ስለማይችል ነው። ከዚህ በመነሳትም ኢኮኖሚው ሊሸከመው የሚችል የመከላከያ በጀትን መመደብ ግድ ይላል፡፡

የሀገራችን መከላከያ በጀት አንድ በመቶ እንኳን ሊሞላ ያልቻለበት ሌላኛው ዋነኛ ምክንያት መከላከያ ሠራዊታችን የድሃ ሀገር ሠራዊት መሆኑን በውል ተገንዝቦ በመንግስት የተመደበለትን በጀት በቁጠባ እያብቃቃ መጠቀምን እንደ ባህል ይዞ የሚሰራ ኃይል ስለሆነ ነው፡፡ የሠራዊታችን በጀትን አብቃቅቶ በመጠቀም የልማት ሃይል እየሆነባቸው ካሉት ዘርፎች ውስጥ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ወጪ ቆጣቢ በማድረግ እንዲሁም ከውጭ ተገዝተው የሚገቡ ቁሳቁሶችን በውስጡ በማምረት የሚያከናውናቸው ተግባራት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከእዚህ ጐን ለጐንም በሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለአብነት ያህል የመከላከያ መሠረተ- ልማት ዘርፍ የተቋሙን የልማት ስራዎች ከመስራት በዘለለ፤ እጅግ አስቸጋሪ በሆኑ ቦታዎች ላይ ለህዝቡ ወሣኝ የሆኑ የመንገድ ፣ የድልድይ፣የመስኖ ልማት ...ወዘተ ቁልፍ ስራዎችን እያከናወነ ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝም በብረታ ብረትና ኢንዱስትሪ ኮርፖርሬሽን ውስጥ የሚገኙ የሠራዊቱ አባላት በታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ ኮርፖሬሽኑ የወሰዳቸውን የሜካኒካል ስራዎች ከውጭ እንዳይገቡና ሀገር ውስጥ እንዲመረቱ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ወጪን የማዳን ተግባራትን ገባራዊ እያደረጉ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም። የኮርፕሬሽኑ ሠራዊት አባላት የትራንስፖርት እጥረትን ለመቅረፍ የከተማ አውቶብሶችንና ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ሀገር ውስጥ በመገጣጠም እንዲሁም የሀገሪቱ ልማት ወሣኝ የሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል እንዳይቆራረጥ ከፍተኛ ሃይል መሸከም የሚችሉ ትራንስፎርመሮችን በመስራት.. ወዘተ ተግባራትን በማከናወን የልማት አጋርነታቸውን በማረጋገጥ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ አብነታዊ ሃቆች የሚያመላክቱት ሠራዊታችን በመንግስት የተመደበለትን በጀት አብቃቅቶ ከመጠቀም ባሻገር በሀገራዊ ልማት ውስጥ እጁን በማስገባት የውጭ ምንዛሪን በማዳን በኢኮኖሚያዊ እመርታችን ላይ ጉልህ አሻራውን እያሳረፈ ነው፡፡ ይህም በአንድ እጁ መሳሪያ በሌላኛው የማልሚያ ቴክኖሎጂዎችን ታጥቆ ለሀገሩ የቆመ ኃይል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

የሠራዊታችን ልማታዊ ኃይልነት በዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት አብነቶች ባሻገር በየዕዙ፣ በየክፍለጦሩና በየሬጅመንቱ በጉልበቱ፣ በገንዘቡ፣ በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና በሌሎች ዘረፎች የልማት አጋርነቱን በተግባር በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡ ሠራዊቱ ለተለያዩ የልማት ስራዎች ከደመወዙ በማዋጣት ከሚያደርገው እገዛ ባሻገር፣ በተሰማራባቸው አካባቢዎች ጊዜውንና ጉልበቱን መስዋዕት በማድረግ የህብረተሰቡን ችግሮች በሚፈቱ ተግባራት ላይ በንቃት እየተሳተፈ ነው፡፡ ሰራዊቱን አስመልክቶ የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በሀገሪቱ ውስጥ ተሰማርቶ በሚገኝባቸው የግዳጅ ቀጣናዎች ሁሉ ለአቅም ደካማ አባወራዎችና አማወራዎች ድጋፍ የመስጠት ስራዎችንም አከናውኗል፤ እያከናወነም ነው፡፡ ማሳቸው ላይ ሰብሎችን በመዝራት በማረም በማጨድና በመሰብሰብ ህዝባዊነቱንና የልማት አጋርነቱን በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡ የአርሶ አደሩ ምርት በፍጥነት ለገበያ እንዲደርስ ለማስቻልም የትራንስፖርት መንገድ በሌላቸው ቦታዎች ከየአካባቢው ህብረተሰብ ጋር እየተቀናጀ በመንገድ ስራ ላይ በንቃት ተሳትፎ በማድረግ ላይም ነው፡፡

ይህ ህዝባዊ ሰራዊት በአንድ እጁ ህገ-መንግስታዊ ተልዕኮውን የሚወጣበት፣ በሌላኛው እጁ ደግሞ ልማትን የሚያከናውንባቸውን ድርብ መሣሪያዎች ይዞ ምንጊዜም ከራሱ በፊት ለህዝብና ለሀገር የቆመው ሠራዊታችን ህዝባዊ ልማታዊነቱ ተዘርዝረው የሚያልቁ አይመስለኝም፡፡ሠራዊቱ ከህብረተሰቡ ጋር አብሮ ስለሚኖርና ችግሩንም ስለሚገነዘብ የሚመደብለትን በጀት በማብቃቃት ከደመወዙ እያዋጣ ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ኬላዎችን፣ መንገዶችን ...ወዘተ በመገንባት እንዲሁም የውስጥ ቁሳቁሶቻቸው እንዲሟላ በማድረግ ለየአካባቢው ህዝብ አስረክቧል፡፡ የአካባቢን ስነ ምህዳር በመጠበቅ ረገድም ከህብረተሰቡ ጋር በመሰለፍ ችግኞችን ተክሏል፣ እንዲፀድቁም በመንከባከብ የድርሻውን እየተወጣ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም መከላከያ ሠራዊታችን ተልዕኮውን በሚወጣባቸው አካባቢዎች በራሱ የውስጥ አቅም፣ ጥረትና ተነሳሽነት ከሚያከናውናቸው የልማት ስራዎች በተጓዳኝ ምግባረ ሰናይ ተግባራትንም ያከናውናል፡፡ በመሆኑም በተለያዩ የሠራዊቱ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ የሠራዊት አባላት ከደመወዛቸው ተቆራጭ እያደረጉ በኤች-አይ-ቪ/ኤድስ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን እንደ ወላጅ አባት ሆነው ያስተምራሉ፤ ይደግፋሉ፡፡ በሀገራችን ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱት ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች በህዝብ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱም ሠራዊታችን ጉልህ አስዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች በደረሰባቸው አካባቢዎች ሠራዊታችን በእግረኛ፣ በኮማንዶና በአየርሃይል ቀድሞ በመድረስ የከፋ ጥፋት እንዳይከሰት በማድረግ የህዝቡን ህይወትና ንብረት በመታደግ ህዝባዊነቱንና የልማት ደጋፊነቱን በማያሻማ መልኩ አረጋግጧል፡፡

ከልማቱ በመለስም በተፈጥሮ የአየር ንብረት መዛባት ምክንያት በተከሰቱት የድርቅ አደጋዎች ሠራዊቱ ከደመወዙ ተቆራጭ በማድረግ ወገኑን ከመደገፉ ባሻገር ለተጐጂው የህብረተሰብ ክፍል ዕርዳታው እንዲደርስለት በተሽከርካሪዎቹ በማጓጓዝ ብሎም ዕርዳታው የሚፈለገው ቦታ እንዲደርስ እጀባ በማድረግ አኩሪ ተግባራትን ፈፅሟል፡፡የሀገራችን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንድ አካል የሆነውን ታላቁን የህዳስ ግድብ ለመገንባት ባለፈው ዓመት መላው የሠራዊታችን አባላትና ሲቪል ሰራተኞች የወር ደመወዛቸውን በዓመት ክፍያ በመፈፀም ቦንድ ገዝተዋል፤ እየገዙም ነው፡፡ ይህም ሰራዊቱ የልማቱ ጠባቂ ብቻ ሣይሆን አልሚ ጭምር መሆኑን የሚያመላክት ነው።

የሠራዊታችን ልማታዊ ተግባር በዚህ ብቻ የተገታ አይደለም። ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ የሚጠይቀውን ሙያተኛ ለማቅረብ ተቋማችን በየከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ የሰው ሃብት

ልማት ስራውን በብቃት በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም ቀደም ሲል በውጭ ሀገር ባለሙያዎች ይከናወኑ የነበሩ የተቋሙ ስራዎች ዛሬ ላይ ሙሉ በሙሉ በሠራዊታችን አባላት እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ይህም ተቋማችን የደረሰበትን ከፍተኛ የሰው ሃይል የማብቃት ስራን አመላካች ነው። ለዚህ አባባሌ በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል። ከመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ተመርቀው የሚወጡ አባላት በመስኩ ውጤት እያመጡ ነው። በሀገሪቱ ውስጥ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ከማስፋፋት ባሻገር ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ ኢንጂነሮችንም ማፍራት ተችሏል። ዛሬ ከኢንጂነሪንግ ኮሌጅ ተመርቀው የሚወጡ የሰራዊቱ አባላት ተቋማዊና ሀገራዊ ችግር ፈቺ በሆኑ መስኮች በመሳተፍ የተጣለባቸውን ተልዕኮ በብቃት በመወጣት ላይ ይገኛሉ። የሠራዊታችንን የውጊያ ቴክኒክን ለማሣደግና ወደ ሚፈለገው የብቃት ደረጃ ለማድረስም በመከላከያ በተከናወኑት ዘርፈ ብዙ ስራዎች በሙያው የሰለጠነ በርካታ የሰው ሃይል ለማግኘት ተችሏል፡፡ይህም ሰራዊቱ አሁንም ይሁን ወደፊት የሚጠብቀውን ግዳጅ በተሟላ የውጊያ ቴክኒክ ታግዞ ህገ-መንግስታዊ ተልዕኮውን አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ እንዲወጣ የሚያስችለው ነው። መከላከያ በራሱ አቅም ሠራዊቱን ሊመሩ የሚችሉ ብቁ አመራሮችን በየደረጃው በማፍራት ላይ ይገኛል። እነዚህ አመራሮች ወታደራዊ ሳይንስና ጥበብን በንድፈ-ሃሳብና በተግባር የተማሩ ከመሆናቸውም በላይ፤ሠራዊታችንን ለድል የሚያበቁትን ወሳኝ አመራር የመስጠት ክህሎት ያላቸው ናቸው።

የመከላከያ ጤና ሳይንስ ኮሌጅም ቢሆን በርካታ ዶክተሮችንና የጤና መኮንኖችን በማፍራት የሠራዊቱን የግዳጅ አወጣጥ በመደገፍ ላይ ይገኛል። መከላከያ በራሱ አቅም የሚያፈራቸው የህክምና ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ የሚያደርጉት ለሰራዊቱ ብቻ ሳይሆን ለሲቪሉ ማህበረሰብም ጭምር ነው። ይህም ጤናማ ህብረተሰብ እንዲኖርና ዜጎች በተጀመረው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ላይ በየደረጃው የበኩላቸውን አስተዋዕኦ እንዲያበረክቱ ያግዛል። ሰራዊቱ የአቅም ግንባታ ማዕከል ሆኖ የኢኮኖሚ ዕድገቱ የሚጠይቀውን ብቃት ያለውን የሰው ሃብት ለሀገርም ጭምር እያፈራ ነው።

በኢፌዴሪ አየር ሃይል በኩልም መከላከያ በርካታ አብራሪዎችን ከማፍራት ጎን ለጎን ከፍተኛ ሀገራዊ የሰው ሃብት ልማትን ዕውን እያደረገ ነው። አየር ሃይሉ ዛሬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። ቀደም ሲል በውጭ ሀገር ዜጎች ይከናወኑ የነበሩ በርካታ ስራዎችን በራሳችን የሰው ሃይል ማከናወን የቻለ ታላቅ ተቋም ነው። የራሱን ቴክኒሽያኖች ከማፍራት በዘለለ

የኢትዮጵያን አየር መንገድ ቴክኒሽያኖችን አሰልጥኖ ያስመረቀበት ደረጃም ላይ ደርሷል። የኢፌዴሪ አየር ሃይል ከተሰጡት ተልዕኮዎቹ አንዱ የሀገሪቱን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ የህዝብና የመንግስት ልማት ተቋማትን ከማንኛውም ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች መከላከልና ማዳን ነው፡፡ ከተልዕኮው በመነሳትም በሀገሪቱ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች በመከላከል ረገድ ዘምን የማይሽራቸውን ስራዎች ሰርቷል፡፡ በዋነኛነትም በደቡብ ክልል በኦሞ ወንዝ ሙላት ባስከተለው ጎርፍ የተጠቁ ዜጎችን በማትረፍ በኩል ከሌሎች የመከላከያ የሠራዊት ሃይል ጋር በጥምረት የሰሩትን ስራ ማስታወስ አንዱ መገለጫ ነው፡፡

በቅርቡም በአዋሽ ወንዝ በደረሰው የጎርፍ አደጋ ቀድሞ በመድረስ የነፍስ አድን ስራ ሰርቷል፡፡ ከዚህም ባሻገር በሀገሪቱ በሚደረጉ የልማት ስራዎች በመሳተፍ ጉልህ ድርሻ ሲወጣ እየተገነቡ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችም ሆኑ ሌሎች የልማት ስራዎች በተገቢው መንገድ እንዲከናወኑ በታጠቃቸው ዘመናዊ ራዳር እና ሚሳይል ኮምፕሌክሶች የ24 ሰዓት ጥበቃ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም በአስተማማኝ የአየር ክልል ዘብነቱን በማረጋገጥ ላይ ነው።

እርግጥ የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ባለፉት 14 የተሃድሶ ዓመታት ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን በአስተማማኝ ለመጠበቅ የሚያስችሉትን ዘርፈ ብዙ ስኬቶችን አስመዝግቧል፡፡ እነዚህ ስኬቶቹ ዛሬ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ክብርና አመኔታን እንዲጎናፀፍ አድርገውታል።

ዛሬ በአንድ ሀገር ውስጥ ግጭት ከተከሰተ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ 'የኢትዮጵያ ሰራዊት እዚህ ቦታ ቢገባ ኖሮ…' እስከማለት የደረሱበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። አዎ! ይህ ህዝባዊ ሃይል ይህን ጥንካሬውን የሚሸረሽረው ምንም ዓይነት ነገር የለም። እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ህዝባዊነቱን፣ የዓላማ ፅናቱን፣ ጀግንነቱንና ጠንካራ ዲሲፕሊኑን ይዞ ሁሌም ጠላቶቻችንና ተላላኪዎቻቸው አንገታቸውን ቀና እንዳያደርጉ ማድረጉ አይቀሬ ነው። ይህን ዕውነታ ደግሞ እነዚህ ከሰላም ጋር የተጣሉ ሃይሎች ሳይቀሩ አብጠርጥረው ያውቁታል። አሁንም ክብርና ሞገስ ለህዝባዊው የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት!